የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# ለዐይነ ሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሑፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣ የማራካሽ ስምምነት የአማርኛ ትርጉም

## Amharic Translation of Marrakesh Treaty to Facilitate Access to Published Works for Persons who are Blind, Visually Impaired, or Otherwise Print Disabled

ሰኔ፣ 2014 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

June 2022
Addis Ababa, Ethiopia

## ምስጋና

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ዐይነ ሥውራን ብሔራዊ ማኅበር ጋር በመተባበር ከዩ.ኤስ.ኤይድ ፍትሕ አክቲቪቲስ ኢን ኢትዮጵያ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ለዐይነ ሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሑፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣ የማራካሽ ስምምነት ትርጉም እትም፡፡

ሰኔ፣ 2014 ዓ.ም.

## ACKNOWLEDGEMENT

ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

The Amharic translation and publication of the Marrakesh Treaty to facilitate access to published works for persons who are blind, visually impaired, or otherwise print disabled was done in collaboration with Ethiopian National Association of the Blind with the financial support of USAID *Feteh* (Justice) Activity in Ethiopia.

June 2022

Feteh (Justice) Activity
IN ETHIOPIA

Ethiopian National
Association of the Blind

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለዐይነ ሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሑፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣውን የማራካሽ ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 1181/2012 በማጽደቁ፤

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችን በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ለመተርጎም እና ለማሰራጨት በአዋጅ ቁጥር 210/1992 አንቀጽ 6 (8) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከኢትዮጵያ ዐይነ ሥውራን ብሔራዊ ማኅበር ጋር በመተባበር ከዩ.ኤስ.ኤይድ ፍትሕ አክቲቪቲስ ኢን ኢትዮጵያ USAID *Feteh* (Justice) Activity in Ethiopia በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ስምምነቱን አስተርጉሞ አሳትሟል።

# ለዐይነ ሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሑፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የወጣ የማራካሽ ስምምነት

ይህ ዓለም አቀፍ ስምምነት የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የቀለም ጽሑፍ ህትመት ሥራዎች ተደራሽነትን ለማመቻቸት የሚያስችል ዓለም አቀፍ ስምምነት ለመፈጸም በተጠራው ዲፕሎማሲያዊ ጉባኤ ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም. ጸድቋል።

# ማውጫ


መቅድም 1

አንቀጽ 1፡ ከሌሎች ቃል ኪዳኖች እና ስምምነቶች ጋር ያለው ግንኙነት 4

አንቀጽ 2፡ ትርጓሜ 4

አንቀጽ 3፡ ስለተጠቃሚ ሰዎች 6

አንቀጽ 4፡ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የሚዘጋጁ ቅጂዎችን በተመለከተ በብሔራዊ ሕጎች ላይ ስለሚኖሩ ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች 7

አንቀጽ 5፡ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎች ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥ 11

አንቀጽ 6፡ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት 14

አንቀጽ 7፡ ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከቱ ግዴታዎች 15

አንቀጽ 8፡ የግል ነጻነትን ስለማክበር 15

አንቀጽ 9፡ ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥን ለማመቻቸት ስለሚደረግ ትብብር 16

አንቀጽ 10፡ ጠቅላላ የአፈጻጸም መርሕዎች 17

አንቀጽ 11፡ ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ አጠቃላይ ግዴታዎች 18

አንቀጽ 12፡ ስለ ሌሎች ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች 20

አንቀጽ 13፡ ስለጉባኤ 20

አንቀጽ 14፡ ዓለም አቀፍ ቢሮ 22

አንቀጽ 15፡ የስምምነቱ ፈራሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች 23

አንቀጽ 16፡ በስምምነቱ የተደነገጉ መብቶች እና ግዴታዎች 23

አንቀጽ 17፡ ስምምነቱን ስለመፈረም 24

አንቀጽ 18፡ ስምምነቱ ተፈጻሚ መሆን ስለሚጀምርበት ጊዜ 24

አንቀጽ 19፡ ስምምነቱን መቀበል ስለሚጸናበት ቀን 24

አንቀጽ 20፡ ከስምምነቱ ስለመውጣት 25

አንቀጽ 21፡ ስለስምምነቱ ቋንቋዎች 25

አንቀጽ 22፡ ስለስምምነቱ ባለአደራ 26

## የኮሚሽነር መልእክት

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ ፌደራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ስር ከተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶቹ መካከል ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት ሰነዶችን በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች መተርጎምና ማሰራጨት ይገኝበታል፡፡ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ዐይነ ሥውራን ብሔራዊ ማኅበር ጋር በመተባበር ስምምነቱ ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን የአማርኛ ትርጉም አዘጋጅቷል፡፡

ለዐይነ ሥውራን፣ የንባብ የዕይታ ችግር ላለባቸው እና በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ አካላዊ ችግር ላለባቸው ሰዎች የህትመት ሥራዎችን ተደራሽነት ለማመቻቸት የወጣው የማራካሽ ስምምነት የህትመት ሥራዎችን በተደራሽና አማራጭ ቅርጽ የማግኘት መብትን በማረጋገጥና የመረጃ ተደራሽነትን በማስፋት ረገድ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ በመገንዘብ የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2012 ዓ.ም. ማጽደቁ ይታወቃል፡፡ ስምምነቱ ዐይነ ሥውራን፣ የማየት ችግር ያለባቸው ወይም ሌሎች የህትመት ጉዳተኞች የቅጂ ወይም የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ያላቸውንም ሆነ የሌላቸውን መጻሕፍት እና ሌሎች የህትመት ሥራዎችን ለመጠቀም የሚገጥሟቸውን የሕግ ክልከላዎች በልዩ ሁኔታ የሚያስቀር ነው፡፡ በተጨማሪም ተዋዋይ መንግሥታት የህትመት ሥራዎችን በተደራሽ አቀራረብ ለማዘጋጀት እና ለማሰራጨት እንዲሁም

የቅጂዎችን ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥ ለማመቻቸት የሚያስችል የቅጂ መብት እና ተዛማጅ መብቶች ልዩ ሁኔታዎችን ወይም ገደቦችን እንዲደነግጉ የሚጠይቅ ነው፡፡

በተጨማሪም ኢትዮጵያ ያጸደቀችው ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነትም ለአካል ጉዳተኞች የመማር እና መረጃን የማግኘት እንዲሁም ከሌሎች ጋር በእኩልነት በባህል፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ሕይወት የመሳተፍ መብትን ግምት ውስጥ በማስገባት በተደራሽ አቀራረብ የሚታተሙ መጻሕፍትን እና ሌሎች የህትመት ሥራዎችን አቅርቦት ለማሳደግ እና በገበያው ውስጥ የሚኖራቸውን ስርጭት ለማሻሻል በተዋዋይ ሀገራት ላይ የሚጥለውን ግዴታ ተግባራዊ የሚያደርግ ሰነድ ነው፡፡

ስምምነቱ ወደ አማርኛ እንዲተረጎም የኢትዮጵያ ዐይነ ሥውራን ብሔራዊ ማኅበር ላደረገው አስተዋፅኦ እንዲሁም ህትመቱን በገንዘብ የደገፈውን ዩኤስኤይድ ፍትሕ አክቲቪቲ ኢን ኢትዮጵያን በኮሚሽኑ ስም አመሰግናለሁ፡፡

ርግበ ገ/ሐዋርያ

የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች ኮሚሽነር

Rigbe Gebrehawaria

# መቅድም

ተዋዋይ ወገኖች፡

በሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ላይ የተደነገጉትን ያለ ማዳላት፣ እኩል እድል የማግኘት፣ የተደራሽነት፣ የተሟላና ውጤታማ ተሳትፎ የማድረግ፣ እና በማኅበረሰብ ውስጥ የመካተት መርሖዎችን በማስታወስ፤

የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች ከሌሎች ጋር በእኩል ደረጃ የተለያዩ መረጃዎችን እና ሐሳቦችን ምርጫቸው በሆነ ማናቸውም የመገናኛ ዘዴ የመፈለግ፣ የመቀበል እና የማስተላለፍ መብቶችን ጨምሮ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን፤ የመማር መብትን እና ጥናትና ምርምር የማድረግ እድልን የሚገድቡ የተሟላ እድገት እንዳያገኙ የሚያደርጉ ተግዳሮቶችን በማጤን፤

የንባብ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች ጨምሮ ሁሉም ሰው በኅብረተሰብ የባህል እንቅስቃሴ ውስጥ የመሳተፍ፣ በኪነ-ጥበባት ሥራዎች የመገልገል፣ ለሳይንስ እድገት አስተዋፅኦ የማድረግና ጥቅሞቹን የመጋራት እድልን ለማጎልበት እንዲሁም ለሥነ-ጥበባዊ ሥራዎች አነሳሽ እና ማበረታቻ ይሆን ዘንድ የቅጂ መብት ጥበቃ አስፈላጊ መሆኑን አጽንኦት በመስጠት፤

የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች በማኅበረሰብ ውስጥ እኩል እድል እንዲኖራቸው በማስቻል ሂደት የህትመት ሥራዎችን በማግኘት ረገድ ያሉባቸውን ተግዳሮቶች እንዲሁም ተደራሽ በሆነ መልክ የተዘጋጁ

ሥራዎችን ቁጥር የመጨመርና ስርጭታቸውን የማሻሻልን አስፈላጊነት በመገንዘብ፤

አብዛኛዎቹ የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች የሚኖሩት በታዳጊ ሀገራት እና ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሀገራት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

ምንም እንኳን በብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግጋት መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም፣ አዳዲስ መረጃዎች እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸውን ሰዎች ሕይወት መሻሻል የሚኖራቸውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሻሻለ የሕግ ማዕቀፍ ሊጠናከር እንደሚችል በመገንዘብ፤

ብዙ አባል ሀገራት በብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግጋቶቻቸው ላይ የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ላሉባቸው ሰዎች ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን ቢደነግጉም ለእነዚህ ሰዎች በቀላሉ መጠቀም በሚያስችል መልክ የተዘጋጁ የህትመት ሥራዎች ቅጂ እጥረት እስካሁን የቀጠለ በመሆኑ፤ እንዲሁም የህትመት ውጤቶችን ለእነዚሁ ሰዎች ተደራሽ ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ሀብት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑና ተደራሽ በሆነ መልክ የተዘጋጁ ቅጂዎች በድንበር ተሻጋሪ ልውውጥ የሚገኙበት እድል ባለመኖሩ ተደራሽ ቅጂዎችን የማዘጋጀት ሥራ ድግግሞሽ መኖሩን በመገንዘብ፣

የቅጂ መብት ባለቤቶች ሥራዎቻቸውን የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ላሉባቸው ሰዎች ተደራሽ በማድረግ ረገድ የሚኖራቸው ሚና አስፈላጊነትንም ሆነ በተለይም ገበያው እንደዚህ ዓይነት ሥራዎችን ማቅረብ በማይችልበት ጊዜ

ሥራዎቹን ለእነዚህ ሰዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ የሆኑ ገደቦች እና የልዩ ሁኔታዎች አስፈላጊነትን በመገንዘብ፣

የደራሲያን መብቶችን ውጤታማነት በመጠበቅ እና በአጠቃላይ የሕዝብ ጥቅም በተለይም በትምህርት፣ በጥናትና ምርምር እና በመረጃ ተደራሽነት መካከል ሚዛን የመጠበቅ አስፈላጊነትን እና እንዲህ ዓይነቱ ሚዛናዊነት የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ላሉባቸው ሰዎች ተጠቃሚነት የሥራዎች ተደራሽነት ውጤታማ እና ወቅታዊ በሆነ መልኩ ማመቻቸት እንደሚገባ በመገንዘብ፤

የቅጂ መብት ጥበቃን በተመለከተ አሁን ባሉት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሰፈሩ የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎችን እና በቅጂ መብት ላይ የሚጣሉ ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን ተቀባይነት በተመለከተ የሥነ ጽሑፍና ኪነ-ጥበባት ሥራዎች ጥበቃን አስመልክቶ በተደረገው የበርን ስምምነት አንቀጽ 9(2) እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች የተደነገገው ባለ ሦስት እርከን መስፈርት አስፈላጊነትን እና ለተለዋዋጭ አሠራር ምቹ መሆኑን ዳግም በማረጋገጥ፤

የልማት እሳቤዎችን የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት አሠራር አካል ለማድረግ ታስቦ በ2007 [እ.ኤ.አ] በዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቁት የልማት አጀንዳ ምክረ ሐሳቦችን አስፈላጊነት በማስታወስ፤

የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ላሉባቸው ሰዎች የህትመት ሥራዎችን ተደራሽ ለማድረግና እንዲጠቀሙባቸው ለማስቻል የዓለም አቀፉ የቅጂ መብት ሥርዓትን ጠቃሚነት፤ እንዲሁም ገደቦችንና ልዩ ሁኔታዎችን ወጥ የማድረግ አስፈላጊነትን በመገንዘብ፤

እንደሚከተለው ተስማምተዋል:-

## አንቀጽ 1

## ከሌሎች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳኖች እና ስምምነቶች ጋር ያለው ግንኙነት

ይህ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሌሎች ስምምነቶች ውስጥ እርስ በእርስ የሚኖራቸውን ማናቸውንም ዓይነት ግዴታዎች የሚሽር ወይም ደግሞ አንድ ተዋዋይ ወገን በማናቸውም ሌሎች ስምምነቶች ያገኛቸውን ማናቸውንም ዓይነት መብቶች ቀሪ የሚያደርግ አይደለም።

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

ለዚህ ስምምነት:-

(ሀ) **"ሥራዎች"** ማለት የሥነ-ጽሑፍና ሥነ-ጥበባዊ ሥራዎችን ለመጠበቅ በወጣው የበርን ስምምነት አንቀጽ 2(1) ሥር በተሰጠው ትርጉም መሠረት በጽሑፍ፣ በማስታወሻ እና/ወይም ተዛማጅ በሆኑ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ በህትመትም ሆነ በሌላ መልክ ተዘጋጅተው በማንኛውም የአቀራረብ ዘዴ በመጠቀም ለሕዝብ የቀረቡ የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-ጥበብ ሥራዎች ናቸው[1]፤

(ለ) **"ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀ ቅጂ"** ማለት ተጠቃሚው ሰው የንባብ፣ የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት

---

1 አንቀጽ 2(ሀ) ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ለዚህ ስምምነት ዓላማ ሲባል ይህ ትርጉም እንደ በድምፅ መልክ የተዘጋጁ መጽሐፍትን ጨምሮ በድምፅ መልክ የተዘጋጁ ሥራዎችን እንደሚያካትት ግንዛቤ ተይዟል።

ለማንበብ ሌላ አካላዊ ችግር እንደሌለበት ሰው ሁሉ አንድን ሥራ በተሻለ ሁኔታና በምቾት እንዲያገኝ መፍቀድን ጨምሮ ተጠቃሚው ሥራውን በቀላሉ ማግኘት በሚያስችለው አማራጭ ዘዴ ወይም መልክ የቀረበ የአንድ ሥራ ቅጂ ማለት ነው። ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀ ቅጂን መጠቀም የሚችሉት በዚህ ስምምነት መሠረት የእንደዚህ ዓይነት ቅጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የታሰቡ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ወጥ ሥራውን በአማራጭ መልክ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ለውጦች እና የተጠቃሚዎችን የተደራሽነት ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጀው ተደራሽ ቅጂ የወጥ ሥራውን ምሉዕነት የጠበቀ መሆን አለበት።

ሐ) **"የተፈቀደለት አካል"** ማለት ትምህርትን፣ ትምህርታዊ ሥልጠናን፣ እንደ ሁኔታው ተለዋዋጭነት ንባብን ወይም የመረጃ ተደራሽነትን ትርፍ በማያስገኝ ሁኔታ ለተጠቃሚ ሰዎች አገልግሎት ለመስጠት በመንግሥት በኩል የተፈቀደለት ወይም ዕውቅና የተሰጠው አካል ማለት ነው። እንዲሁም እንደ አንድ ተቀዳሚ ተግባሩ ወይም ተቋማዊ ግዴታዎቹ ለተጠቃሚ ሰዎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን የሚያቀርብ የመንግሥት ተቋምን ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅትን ያካትታል[2]።

የተፈቀደለት አካል ራሱ የሚከተለውን የአሠራር ሥርዓት የሚዘረጋው፡-

2 አንቀጽ 2(ሐ) ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ለዚህ ስምምነት ዓላማ ሲባል "በመንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸው አካላት" ትምህርትን፣ ትምህርታዊ ልጠናን፣ ተስማሚ የንባብ አገልግሎት ወይም የመረጃ ተደራሽነትን ትርፍ በማያስገኝ ሁኔታ ለተጠቃሚ ሰዎች አገልግሎት ለመስጠት ከመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ አካላትን ሊያካትት እንደሚችል ግንዛቤ ተይዟል።

(i) የሚያገለግላቸው ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የታሰቡ ሰዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤

(ii) ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ የቅጂ ሥራዎች ስርጭት እና ተደራሽነትን ለተጠቃሚ ሰዎች እና/ወይም ለተፈቀደላቸው አካላት ብቻ የተወሰነ ለማድረግ፤

(iii) ያልተፈቀደ የቅጂዎች ብዜትን፣ ስርጭትን እና ተደራሽ የማድረግ ተግባራትን ላለማበረታታት፤ እና

(iv) በአንቀጽ 8 በተደነገገው መሠረት የተጠቃሚ ሰዎችን የግል ነጻነት ባከበረ መልኩ የሥራዎች ቅጂዎችን በአግባቡ ለመመዝገብ እና አያያዛቸውንም ጥንቃቄ የተሞላበት ለማድረግ ይሆናል።

## አንቀጽ 3

## ስለተጠቃሚ ሰዎች

ተጠቃሚ ሰው ማለት፤

ሌሎች ማናቸውም የአካል ጉዳት ዓይነቶች እንዳሉ ሆነው፡-

(ሀ) ዐይነ ሥውር የሆነ፤

(ለ) የማየት እክል ወይም ጽሑፎችን በቀላሉ የመገንዘብ ወይም የማንበብ ችግር ያለበት ሆኖ የማየት እክል ወይም ጉዳት እና የማንበብ ችግር ከሌለበት ሰው ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ የማየት አቅሙን ለማሻሻል የማይቻል በመሆኑ ምክንያት የህትመት ሥራዎችን የማየት እክል ወይም ጉዳት ከሌለበት

ሰው ጋር በመሠረታዊነት ተመሳሳይ በሆነ ደረጃ ለማንበብ የማይችል፤ ወይም[3]

(ሐ) በሌላ አካላዊ ጉዳት መንሥኤነት መጽሐፍትን ለመያዝ ወይም ለመጠቀም ወይም ለማንበብ በተለምዶ ተቀባይነት ባለው መጠን ለማተኮር ወይም ዐይኖቹን ለማንቀሳቀስ የማይችል ሰው ነው።

## አንቀጽ 4

## ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን በተመለከተ በብሔራዊ ሕጎች የሚደነገጉ ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች

(ሀ) ተዋዋይ ወገኖች የሥራዎችን ቅጂ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ ለተጠቃሚ ሰዎች በቀላሉ ለማቅረብ እንዲቻል በዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት በተደነገገው መሠረት የማባዛት መብትን፣ የማሰራጨት መብትን፣ እንዲሁም ለሕዝብ የማቅረብ መብትን አስመልክቶ ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን በብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግጋቶቻቸው ማካተት አለባቸው። በብሔራዊ ሕግ የሚደነገገው ገደብ ወይም ልዩ ሁኔታ ሥራውን በአማራጭ ቅርጽ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ለውጦችን መፍቀድ አለበት።

3 አንቀጽ 3(ለ)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- በዚህ ድንጋጌ አገላለጽ መሠረት “ሊሻሻል የማይችል” ሲባል ሁሉንም ሊኖሩ የሚችሉ የሕክምና ምርመራ ሂደቶችን እና ሕክምናዎችን አሟጦ የመጠቀም አንድምታ የለውም።

(ለ) በተጨማሪም ተዋዋይ ወገኖች ሥራዎችን ለተጠቃሚ ሰዎች እንዲደርሱ ለማመቻቸት ሲባል ሥራዎችን ለሕዝብ የማቅረብ መብት ላይ ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን ሊደነግጉ ይችላሉ።

1. አንድ ተዋዋይ ወገን በአንቀጽ 4(1) ሥር የተመለከተውን ግዴታ በራሱ ብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግ ለሁሉም መብቶች ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን ከዚህ ቀጥሎ በተገለጸው ሁኔታ በመደንገግ ሊያወጣ ይችላል።

   (ሀ) የተፈቀደላቸው አካላት ከቅጂ መብት ባለቤቱ ፈቃድ ውጪ የሥራዎችን ቅጂ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ እንዲያዘጋጁ፣ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀ ቅጂን ከሌላ የተፈቀደለት አካል እንዲያገኙ፣ እና እነዚህን ቅጂዎች ንግድን ዓላማ ባላደረገ ሁኔታ ማዋስን ወይም በሽቦ ወይም ሽቦ አልባ የኤሌክትሮኒክስ የግንኙነት መንገዶችን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ ለተጠቃሚ ሰዎች እንዲያቀርቡ፤ እንዲሁም እነዚህን ዓላማዎች ማሳካት የሚያስችሉ ማናቸውንም አስፈላጊ ተግባራት የማከናወን ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል። የተፈቀደለት አካል እነዚህን ተግባራት ማከናወን የሚችለው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁሉም ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።

      (i) የተባለውን ተግባር ለማከናወን የሚፈልገው የተፈቀደለት አካል ሥራውን ወይም

የሥራውን ቅጂ በሕጋዊ መንገድ ያገኘው ከሆነ፤

(ii) ሥራው ተደራሽ ወደሆነ ቅጂ ከተለወጠ፤ ተደራሽ የሆነውን ቅጂ ለመጠቀም የሚያስችሉ አስፈላጊ ገጽታዎች ሊካተትበት ይችላል፤ ሆኖም ግን ሥራውን ለተጠቃሚው ሰው ተደራሽ ለማድረግ ከሚያስፈልጉት ለውጦች ውጪ ያሉ ለውጦችን የሚያካትት መሆን የለበትም፤

(iii) እንደዚህ ያሉ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጅዎች የሚቀርቡት በዚህ ስምምነት መሠረት የመብት ተጠቃሚ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ከሆነ፤

(iv) ተግባሩ የሚከናወነው ትርፍን መሠረት ባላደረገ ሁኔታ ከሆነ፤

እና

(ለ) አንድ ተጠቃሚ ሰው ወይም የቅርብ ተንከባካቢውን ወይም ጠባቂውን ጨምሮ እርሱን ወይም እርሷን ተክቶ የሚሠራ ሰው የህትመት ሥራን ለተጠቃሚው ሰው የግል አገልግሎት ተደራሽ በሆነ ቅርጽ ሊያዘጋጅ ወይም ተጠቃሚው ሰው ይህንኑ እንዲያዘጋጅ እና እንዲገለገል ሊረዳው ይችላል። ይህም የሚሆነው

ተጠቃሚው ሰው ሥራውን ወይም የሥራውን ቅጂ በሕጋዊ መንገድ ያገኘው ከሆነ ነው።

2. አንድ ተዋዋይ ወገን በአንቀጽ 10 እና 11 መሠረት በራሱ ብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግ ውስጥ ሌሎች ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን በመደንገግ አንቀጽ 4(1) ን አሚልቶ ሊፈጽም ይችላል[4]።

3. አንድ ተዋዋይ ወገን በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚ ሰዎች ከገበያ መገኘት የማይችሉ በተለይም ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ሥራዎችን በተመለከተ ይህን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎች ሊወስን ይችላል። ይኸን የሚያደርግ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን ይህንን ስምምነት በሚያጸድቅበት፣ በሚቀበልበት ወይም ዘግይቶ በሚቀላቀልበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ ባለ በማንኛውም ጊዜ በዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዘንድ በሚቀመጥ የማሳወቂያ ደብዳቤ ይህንኑ ማሳወቅ አለበት[5]።

---

4 አንቀጽ 4(3) ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ይህ አንቀጽ የመተርጎም መብትን (የዕይታ ችግር ወይም በመደበኛ የንባብ ስልት ለማንበብ ሌሎች አካላዊ ችግሮች ያሉባቸውን) አስመልክቶ በበርን ስምምነት የተፈቀዱ የገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች የተፈጻሚነት ወሰንን የሚቀንስ ወይም የሚጨምር እንዳልሆነ ግንዛቤ ተይዟል።

5 አንቀጽ 4(4)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ከገበያ የሚገኝ የሚለው መስፈርት በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ገደብ ወይም ልዩ ሁኔታ ከባለ ሦስት ደረጃ መስፈረት ጋር የሚስማማ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመበየን ከግምት ውስጥ እንደማይገባ ግንዛቤ ተይዟል።

4. በዚህ አንቀጽ ሥር የተደነገጉ ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎች ዋጋ የሚከፈልባቸው መሆን ወይም አለመሆናቸውን የመወሰን ጉዳይ የብሔራዊ ሕግ ጉዳይ ነው።

## አንቀጽ 5

## ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችና ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥ

1. ተዋዋይ ወገኖች ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀ ቅጂ በገደብ ወይም በልዩ ሁኔታ ወይም በሕግ የአፈጻጸም ሥርዓት መሠረት ከተዘጋጀ፤ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀውን ቅጂ በተፈቀደለት አካል በኩል ለተጠቃሚው ሰው ወይም በሌላ ተዋዋይ ወገን ውስጥ ላለ የተፈቀደለት አካል እንዲደርስ እንዲደረግ መደንገግ አለባቸው[6]።

2. አንድ ተዋዋይ ወገን በራሱ ብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግ ውስጥ እንደሚከተሉት ያሉ ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን በመደንገግ አንቀጽ 5(1)ን ሊያሟላ ይችላል፡-

   (ሀ) የተፈቀደላቸው አካላት ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀ ቅጂን ከባለመብቱ ፈቃድ ውጪ ተጠቃሚ ሰዎች ብቻ እንዲጠቀሙበት በሌላ ተዋዋይ ወገን ውስጥ ላለ የተፈቀደለት አካል የማሰራጨት ወይም የማቅረብ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፤ እንዲሁም

[6] አንቀጽ 5(1)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- በተጨማሪም በዚህ ስምምነት ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎች በማንኛውም ሌላ ስምምነት መሠረት የተገኙ በብቸኝነት የመጠቀም መብቶች (exclusive rights) ወሰንን የሚቀንስ ወይም የሚጨምር እንዳልሆነ ግንዛቤ ተይዟል።

(ለ) የተፈቀደላቸው አካላት ከባለመብቱ ፈቃድ ውጪ እና በአንቀጽ 2(ሐ) መሠረት ተደራሽነት ባለው መልክ የተዘጋጀ ቅጂን በሌላ ተዋዋይ ወገን ውስጥ ላለ ተጠቃሚ ሰው የማሰራጨት ወይም የማቅረብ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል።

ሆኖም ግን፣ ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀን ቅጂ ማሰራጨት ወይም ማቅረብ የሚፈልገው የተፈቀደለት አካል ከማሰራጨቱ ወይም ከማቅረቡ በፊት ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጀው ቅጂ ከተጠቃሚ ሰዎች ውጪ ጥቅም ላይ እንደሚውል የማያውቅ ወይም ለማወቅ በቂ ምክንያት የሌለው ሊሆን ይገባል[7]።

3. አንድ ተዋዋይ ወገን በአንቀጽ 5(4)፣ 10 እና 11 መሠረት በራሱ ብሔራዊ የቅጂ መብት ሕግ ውስጥ ሌሎች ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን በመደንገግ አንቀጽ 5(1)ን ሊያሟላ ይችላል።

4.

(ሀ) በተዋዋይ ወገን ውስጥ ያለ አንድ የተፈቀደለት አካል በአንቀጽ 5(1) መሠረት ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን ሲቀበል እና በበርን ስምምነት አንቀጽ 9

---

7 አንቀጽ 5(2)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ:- ተደራሽነት ባለው ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን በሌላ ተዋዋይ ወገን ውስጥ ለሚገኝ ተጠቃሚ ሰው በቀጥታ ለማሰራጨት ወይም ተደራሽ ለማድረግ ሲሠራ አገልግሎቱ የሚሰጠው ሰው ትክክለኛው ተጠቃሚ ሰው ስለመሆኑ የተፈቀደለት አካል የማረጋገጥ ሥራዎች መሥራት እና በአንቀጽ 2(ሐ) በተገለጸው መሠረት የራሱን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱ ተገቢ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ተይዟል።

ሥር በዚሁ ተዋዋይ ወገን ላይ የተጣሉ ግዴታዎች ከሌሉ፣ ከራሱ የሕግ ሥርዓትና አሠራር ጋር በሚስማማ ሁኔታ ተደራሽነት ባለው መልክ የተዘጋጁ ቅጂዎች የሚባዙት፣ የሚሰራጩት ወይም ተደራሽ የሚሆኑት በተዋዋዩ ወገን የግዛት ክልል ውስጥ ለሚገኙ ተጠቃሚ ሰዎች አገልግሎት ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል።

(ለ) ተዋዋዩ ወገን የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት አካል ካልሆነ በስተቀር ወይም ደግሞ ሥራውን በአግባቡ ከመጠቀም መደበኛ አሠራር ጋር ለማይቃረኑ እና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የባለመብቱን ሕጋዊ ጥቅሞች ለማይጎዱ ለተወሰኑ ልዩ ጉዳዮች ይህን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ሥራውን በማሰራጨት መብት እና ለሕዝብ በማቅረብ መብት ላይ ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን ካልወሰነ በስተቀር፤ በአንቀጽ 5(1) መሠረት ተደራሽነት ባለው መልክ የተዘጋጁ ቅጂዎችን በተፈቀደለት አካል ማሰራጨቱ እና ተደራሽ እንዲሆኑ የሚደረገው በዚያ ተዋዋይ ወገን የግዛት ክልል የተወሰነ ይሆናል[8; 9]።

---

8 አንቀጽ 5(4) (ለ)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- አንድ ተዋዋይ ወገን በዚህ ስምምነት ወይም በሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ካሉበት ግዴታዎች ባለፈ የባለሦስት ደረጃ መስፈረትን እንዲተገብር ይህ ስምምነት እንደማይጠይቅ ወይም እንደዚያ ያለ አንደምታ እንደሌለው ግንዛቤ ተይዟል።

9 አንቀጽ 5(4) (ለ)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ይህ ስምምነት አንድ ተዋዋይ ወገን የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነትን እንዲያጸድቅ ወይም እንዲቀላቀል ወይም ማንኛውንም ድንጋጌዎቹን እንዲያከብር ምንም ዓይነት ግዴታዎችን እንደማይፈጥር፤

(ሐ) **የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የማሰራጨት ወይም ለሕዝብ ተደራሽ የማድረግ ምንነትን በተመለከተ መወሰንን የመከልከል ውጤት አይኖራቸውም።**

**የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች በአእምሯዊ ፈጠራ መብት ጥበቃ ሕግና አሠራር አግባብ የመብት መሟጠጥ የሚለውን ጉዳይ** (exhaustion of rights or first sale doctrine) **አይመለከቱም።**

## አንቀጽ 6

## ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት

**አንድ ተጠቃሚ ሰው፣ እርሱን ወይም እርሷን ተክቶ የሚሠራ ሰው፣ ወይም አንድ የተፈቀደለት አካል የሥራ ቅጅን ተደራሽ በሆነ ቅርጽ እንዲያዘጋጅ የአንድ ተዋዋይ ወገን ብሔራዊ ሕግ በሚፈቅድለት መጠን ልክ ለተጠቃሚ ሰዎች ጥቅም ሲባል ከባለመብቱ ፈቃድ ውጪ ተደራሽነት ባለው መልክ የተዘጋጀ ቅጂን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገቡ የተዋዋይ ወገኑ ብሔራዊ ሕግ መፍቀድ አለበት[10]።**

---

እንዲሁም ይህ ስምምነት በዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ማናቸውንም መብቶችን፣ ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን የመለወጥ ውጤት እንደሌለው ግንዛቤ ተይዟል።

10 አንቀጽ 6ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- ተዋዋይ ወገኖች በአንቀጽ 6 የተመለከተውን ግዴታቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በአንቀጽ 4 ሥር የተመለከቱት የአሠራር ምቹነት/ተለዋዋጭነት (አሠራርን እንዳስፈላጊነቱ መለዋወጥ) ዕድል እንዳሏቸው ግንዛቤ ተይዟል።

## አንቀጽ 7

## በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከቱ ግዴታዎች

ተዋዋይ ወገኖች ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚፈጸሙ የማጭበርበር ተግባሮችን ለመከላከል በቂ የሕግ ጥበቃና መፍትሄዎችን በሚደነግጉበት ጊዜ ይኸው የሕግ ጥበቃ ተጠቃሚ ሰዎች በዚህ ስምምነት በተደነገጉ ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንዳያደርጋቸው እንደአስፈላጊነቱ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው[11]።

## አንቀጽ 8

## የግል ነጻነትን ስለማክበር

በዚህ ስምምነት ውስጥ የተደነገጉት ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ ተዋዋይ ወገኖች የተጠቃሚ ሰዎችን የግል ነጻነት ከሌሎች ጋር እኩል በሆነ ሁኔታ ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

[11] አንቀጽ 7ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ፡- የተፈቀደላቸው አካላት በተለያዩ ሁኔታዎች ተደራሽነት ባለው መልክ የሚቀርቡ ቅጂዎችን በማዘጋጀት፣ በማሰራጨት እና ተደራሽ በማድረግ ረገድ ቴክኖሎጂያዊ እርምጃዎችን መርጠው ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉና ይህም የሚሆነው በብሔራዊ ሕግ መሠረት ከሆነ ይህ ድንጋጌ እንደዚህ ዓይነት አሠራሮችን እንደማይከለክል ግንዛቤ ተይዟል።

# አንቀጽ 9

## ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥን ለማመቻቸት ስለሚደረግ ትብብር

1. ተዋዋይ ወገኖች የተፈቀደላቸው አካላት እርስ በእርሳቸው እንዲተዋወቁ በመደገፍ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመረጃ መጋራትን በማበረታታት ተደራሽ በሆነ ቅርጽ የተዘጋጁ ቅጂዎችን ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥ ለማሳለጥ ጥረት ማድረግ አለባቸው። የዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዓለም አቀፍ ቢሮም ለዚሁ ዓላማ የሚያገለግል የመረጃ ቋት ማዘጋጀት አለበት።

2. በአንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ተግባራት ላይ የተሰማሩ የተፈቀደላቸው አካላት በአንቀጽ 2(ሐ) መሠረት የዘረጓቸውን አሠራሮች በተመለከተ መረጃዎችን ተደራሽ እንዲያደርጉ ተዋዋይ ወገኖች ተስማምተዋል። መረጃን ተደራሽ ማድረጉ የሚከናወነው በተፈቀደላቸው አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ በማድረግ እንዲሁም የተከናወኑ ድንበር-ዘለል የተደራሽ ቅጂዎች ልውውጥን ጨምሮ ፖሊሲዎቻቸውን እና አሠራሮቻቸውን በተመለከተ እንደአግባቡ መረጃውን ለሚፈልጉ ወገኖች እና ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ነው።

3. የዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዓለም አቀፍ ቢሮ ይህ ስምምነት እንዴት እየተተገበረ እንደሆነ የሚያመለክቱ መረጃዎችን ባገኘ ጊዜ ሁሉ ማጋራት ይችላል።

4. ተዋዋይ ወገኖች የዚህን ስምምነት ዓላማና ግቦች እውን ለማድረግ ሲባል በብሔራዊ ደረጃ የሚከናወኑ ጥረቶችን የሚደግፍ ዓለም አቀፍ ትብብር መኖርና መስፋፋት አስፈላጊነትን ይገነዘባሉ[12]።

## አንቀጽ 10

## አተገባበርን የተመለከቱ ጠቅላላ መርሕዎች

1. ተዋዋይ ወገኖች የዚህን ስምምነት ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተስማምተዋል።

2. ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ስምምነት የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ተገቢውን የአሠራር ዘዴ በራሳቸው የሕግ ሥርዓትና አሠራር መሠረት ከመወሰን የሚከለክላቸው ነገር የለም[13]።

3. ተዋዋይ ወገኖች በተለይም ለተጠቃሚ ሰዎች ጥቅም ሲባል የሚደረጉ ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን፣ ሌሎች ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን፣ ወይም ሁለቱን በማጣመር፣

---

12 አንቀጽ 9ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ:- አንቀጽ 9 የተፈቀደላቸው አካላት እንዲመዘገቡ የሚያስገድድ ወይም የተፈቀደላቸው አካላት በዚህ ስምምነት በተጠቀሱ ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ቅድመ ሁኔታ እንደማያስቀምጥ፤ ነገር ግን ተደራሽነት ባለው መልክ የሚዘጋጁ ቅጂዎች ድንበር ተሻጋሪ ልውውጥን ለማመቻቸት መረጃን የማጋራት ዕድል እንደሚሰጥ ግንዛቤ ተይዟል።

13 አንቀጽ 10(2)ን በተመለከተ የስምምነት መግለጫ:- በድምፅ መልክ ያሉ ሥራዎችን ጨምሮ አንድ ሥራ በአንቀጽ 2(ሀ) አገባብ እንደ ሥራ የሚቆጠር ከሆነ በዚህ ስምምነት ውስጥ የተደነገጉት ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች ሁሉ የሥራ ቅጂን ተደራሽነት ባለው መልክ ለማዘጋጀት፣ ለማሰራጨት እና ለተጠቃሚ ሰዎች ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊ በሆኑ ተዛማጅነት ባላቸው መብቶች ላይ እንዳግባቡ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ግንዛቤ ተይዟል።

በብሔራዊ የሕግ ሥርዓታቸውና አሠራራቸው ውስጥ በመደንገግ በዚህ ስምምነት የተመለከቱ መብቶቻቸውን ሊጠቀሙ እና ግዴታዎቻቸውን ሊወጡ ይችላሉ። እነዚህም በበርን ስምምነት፣ በሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በአንቀጽ 11 ሥር ከተደነገጉት የተዋዋይ ወገኖች መብቶች እና ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ለተጠቃሚ ሰዎች ጥቅም ሲባል ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንደ ፍትሓዊ አሠራሮች፣ ድርድሮች ወይም አጠቃቀሞች ባሉ ጉዳዮች ላይ የሚተላለፉ የፍርድ ቤት፣ አስተዳደራዊ ወይም የቁጥጥር ውሳኔዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## አንቀጽ 11

## ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን የተመለከቱ ጠቅላላ ግዴታዎች

አንድ ተዋዋይ ወገን የዚህን ስምምነት ተግባራዊነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሚወስድበት ጊዜ በበርን ስምምነት፣ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ስምምነት እና በዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት (የእነዚህኑ የትርጓሜ ስምምነቶችን ጨምሮ) መሠረት ያሉትን መብቶች ሊጠቀምባቸው ይችላል፣ ግዴታዎቹንም መወጣት አለበት። ሆኖም ግን:-

(ሀ) በበርን ስምምነት አንቀጽ 9(2) መሠረት አንድ ተዋዋይ ወገን የህትመት ሥራዎች በተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች እንዲባዙ ሊፈቅድ ይችላል፤ ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ማባዛት አንድን ሥራ በአግባቡ ከመጠቀም መደበኛ አሠራር ጋር የሚቃረን

እና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የደራሲውን ሕጋዊ ጥቅሞች የሚጎዳ መሆን የለበትም፤

(ለ) ከንግድ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የአእምሯዊ ንብረት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 13 መሠረት አንድ ተዋዋይ ወገን ሥራን በተለመደው ሁኔታ ከመጠቀም መደበኛ አሠራር ጋር በማይቃረን እና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የባለመብቱን ሕጋዊ ጥቅሞች በማይጎዱ በተወሰኑ ልዩ ጉዳዮች በብቸኝነት የመጠቀም መብት ላይ ባሉ ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎች የተወሰነ ይሆናል፤

(ሐ) በዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት አንቀጽ 10(1) መሠረት አንድ ተዋዋይ ወገን ሥራን በተለመደው ሁኔታ ከመጠቀም መደበኛ አሠራር ጋር በማይቃረኑ እና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የደራሲውን ሕጋዊ ጥቅሞች በማይጎዱ የተወሰኑ ልዩ ጉዳዮች ላይ በዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት መብት በተሰጣቸው ደራሲያን ላይ ገደቦችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን ሊደነግግ ይችላል፤

(መ) በዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት የቅጂ መብት ስምምነት አንቀጽ 10(2) መሠረት አንድ ተዋዋይ ወገን የበርን ስምምነትን ተግባራዊ በሚያደርግበት ጊዜ በመብቶች ላይ ገደቦች ወይም ልዩ ሁኔታዎችን ሥራን በተለመደው ሁኔታ ከመጠቀም መደበኛ አሠራር ጋር በማይቃረኑ እና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የደራሲውን ሕጋዊ ጥቅሞች በማይጎዱ በተወሰኑ ልዩ ጉዳዮች መሆን አለበት።

## አንቀጽ 12

## ሌሎች ገደቦች እና ልዩ ሁኔታዎች

1. አንድ ተዋዋይ ወገን የራሱን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እና ማኅበራዊና ባህላዊ ፍላጎቶቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ያደገ ሀገርን በተመለከተ ልዩ ፍላጎቶቹን እና የተለዩ ዓለም አቀፋዊ መብቶቹን እና ግዴታዎቹን እና ለአሠራር ምቹነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ ከተዋዋይ ወገኑ ዓለም አቀፋዊ መብቶችና ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ፤ ለተጠቃሚ ሰዎች ጥቅም ሲባል በዚህ ስምምነት ከተደነገጉት ውጪ በራሱ ብሔራዊ ሕግ ሌሎች የቅጂ መብት ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚችል ተዋዋይ ወገኖች ይገነዘባሉ።

2. ይህ ስምምነት በአካል ጉዳተኝነት ላይ በብሔራዊ ሕግ የተደነገጉ ሌሎች ገደቦችን እና ልዩ ሁኔታዎችን አያስቀርም።

## አንቀጽ 13

## ስለጉባኤ

1. (ሀ) ተዋዋይ ወገኖች ጉባኤ ይኖራቸዋል።

   (ለ) እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በተለዋጭ ልዑካን፣ በአማካሪዎች እና በባለሙያዎች ሊታገዝ በሚችል አንድ ልዑክ በጉባኤው ላይ ይወከላል።

(ሐ) ለእያንዳንዱ ልዑክ የሚያስፈልግ ወጪ ውክልናውን በሰጠው የተዋዋይ ወገን በኩል የሚሸፈን ይሆናል። ጉባኤው የተባበሩት መንግሥታት የጠቅላላ ጉባኤ አሠራርን በመከተል በማደግ ላይ ያሉ ተብለው ለሚታወቁ ሀገራት ወይም ወደ ገበያ ኢኮኖሚ በመሸጋገር ላይ ካሉ ሀገራት የሆኑ ተዋዋይ ወገኖችን ልዑኮች የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማመቻቸት የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅትን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግለት ሊጠይቅ ይችላል።

2. (ሀ) ጉባኤው የዚህን ስምምነት ዘላቂነት እና እድገት እንዲሁም የዚህን ስምምነት አተገባበር እና አሠራር በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል።

(ለ) ጉባኤው የተወሰኑ የበይነ-መንግሥታዊ ድርጅቶች የዚህ ስምምነት አካል እንዲሆኑ አዲስ አባል መቀበልን በተመለከተ በአንቀጽ 15 ሥር የተሰጠውን ተግባር ያከናውናል።

(ሐ) ጉባኤው ይህንን ስምምነት ለማሻሻል ማንኛውንም ዲፕሎማሲያዊ ስብሰባ እንዲካሄድ ይወስናል እንዲሁም ለዚሁ ዲፕሎማሲያዊ ስብሰባ ዝግጅት አስፈላጊ ዝግጅት እንዲደረግ ለዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ትእዛዝ ይሰጣል።

3. (ሀ) መንግሥት የሆነ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን አንድ ድምፅ ይኖረዋል፤ እንዲሁም በራሱ ስም ብቻ ድምፅ ይሰጣል።

(ለ) የበይነ-መንግሥታዊ ድርጅት የሆነ ማንኛውም ተዋዋይ ወገን በአባል ሀገራት ምትክ የዚህ ስምምነት አካል በሆኑት የድርጅቱ አባል ሀገራት ቁጥር ጋር እኩል በሆነ የድምፅ መጠን ልክ ድምፅ በመስጠት ሊሳተፍ ይችላል። ከድርጅቱ አባል ሀገራት መካከል ማንኛውም አንድ ሀገር ድምፅ የመስጠት መብቱን ራሱ የሚጠቀምበት እንደሆነ የበይነ-መንግሥታዊ ድርጅቱ ድምፅ በመስጠት ላይ ሊሳተፍ አይችልም። ሲገለበጥም ውጤቱ የዚሁ ተቃራኒ ይሆናል።

4. የጉባኤው ስብሰባ በዋና ዳይሬክተሩ የሚጠራ ሲሆን የተለዩ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር ከዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ እና በተመሳሳይ ቦታ ይካሄዳል።

5. ጉባኤው ውሳኔዎቹን በስምምነት ለማሳለፍ ይጥራል፣ እንዲሁም የምልአተ ጉባኤ ስለመሟላት እና የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለተለያዩ ዓይነት ውሳኔዎች ስለሚያስፈልግ የአብላጫ ድምፁን ጨምሮ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ስለሚጠራበት ሁኔታ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል።

## አንቀጽ 14

## ዓለም አቀፍ ቢሮ

የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዓለም አቀፍ ቢሮ ይህንን ስምምነት የተመለከቱ አስተዳደራዊ ተግባራትን ያከናውናል።

## አንቀጽ 15

## የስምምነቱ አካል ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

1. ማንኛውም የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት አባል ሀገር የዚህ ስምምነት አካል ሊሆን ይችላል።

2. ጉባኤው ማንኛውም በይነ-መንግሥታዊ ድርጅት በዚህ ስምምነት የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ በሁሉም የአባል ሀገራቶቹ ላይ የራሱ የሆነ አስገዳጅ ሕግ ያለው ስለመሆኑ እና ባለው ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መሠረት የዚህ ስምምነት አካል ለመሆን በአግባቡ የተፈቀደለት ስለመሆኑ በማረጋገጥ፤ እንዲሁም በስምምነቱ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ብቁ መሆኑን በመግለጽ የዚህ ስምምነት አካል እንዲሆን ለመቀበል ሊወስን ይችላል።

3. የአውሮፓ ኅብረት ይህን ስምምነት ባጸደቀው የዲፕሎማሲያዊ ስብሰባ ላይ ከላይ የተመለከተውን መግለጫ ያሳወቀ በመሆኑ የዚህ ስምምነት አካል ሊሆን ይችላል።

## አንቀጽ 16

## በስምምነቱ ስለተደነገጉ መብቶች እና ግዴታዎች

በዚህ ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በዚህ ስምምነት ውስጥ ያሉ ሁሉንም መብቶች የመጠቀም እና ሁሉንም ግዴታዎች የመቀበል ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 17

## ስምምነቱን ስለመፈረም

ይህ ስምምነት ከጸደቀ በኋላ ለአንድ ዓመት ለማንኛውም ብቁ ለሆነ ወገን ፊርማ በማራካሽ ዲፕሎማሲያዊ ስብሰባ እና ከዚያ በኋላም በዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ክፍት ሆኖ ይቆያል።

## አንቀጽ 18

## የስምምነቱ ተፈፃሚ መሆን ስለሚጀምርበት ጊዜ

ይህ ስምምነት በአንቀጽ 15 በተጠቀሰው መሠረት ብቁ የሆኑ 20 ፈራሚ አካላት የማጽደቂያ ወይም ዘግይቶ የመቀበያ ሰነዶቻቸውን ካስገቡ ከሦስት ወር በኋላ በሥራ ላይ ይውላል።

## አንቀጽ 19

## ስምምነቱን መቀበል ስለሚጸናበት ቀን

ይህ ስምምነት በሚከተሉት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል:-

(ሀ) ይህ ስምምነት በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአንቀጽ 18 ሥር በተጠቀሱ ብቁ በሆኑ 20 ተፈራራሚ አካላት ላይ፤

(ለ) በአንቀጽ 15 ሥር በተመለከተው መሠረት ብቁ በሆነ በእያንዳንዱ ሌላ አካል ላይ፤ ይኸው አካል ስምምነቱን ያጸደቀበትን ወይም ዘግይቶ የተቀበለበትን ሰነድ ለዓለም

አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ካስረከበበት ቀን ከሦስት ወር ጊዜ በኋላ።

## አንቀጽ 20

## ከስምምነቱ ስለመውጣት

ማንኛውም የዚህ ስምምነት ተዋዋይ ወገን ለዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር በሚላክ ማስታወቂያ መሠረት ከስምምነቱ ሊወጣ ይችላል። ከስምምነቱ መውጣት ውጤት የሚኖረው የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ማስታወቂያውን ከተቀበለበት ቀን ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል።

## አንቀጽ 21

## ስለስምምነቱ ቋንቋዎች

1. ይህ ስምምነት በእንግሊዝኛ፣ በአረብኛ፣ በቻይንኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በሩስያኛ እና በስፓኝ ቋንቋዎች በአንድ ዋና ቅጂ ላይ የተፈረመ ሲሆን እነዚህ ሁሉም ትክክለኛ ቅጂ ተደርገው ይወሰዳሉ።

2. ጥቅም ያለው አካል በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ይመለከተናል ከሚሉ ከሁሉም አካላት ጋር ከተማከረ በኋላ በስምምነቱ አንቀጽ 21(1) ሥር ከተጠቀሱት ቋንቋዎች በተጨማሪ በሌላ የሥራ ቋንቋ ተቋማዊ ጽሑፍ ያዘጋጃል። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ “ጥቅም ያለው አካል” ማለት የሥራ ቋንቋው ወይም

ከሥራ ቋንቋዎቹ መካከል አንዱን ቋንቋ የተጠቀመ ማንኛውም የዓለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት አባል ሀገር፣ እና የአውሮፓ ኅብረት፣ እንዲሁም የዚህ ስምምነት አካል ሊሆን የሚችልና ከሥራ ቋንቋዎቹ መካከል አንዱን ቋንቋ የተጠቀመ ማንኛውም በይነ-መንግሥታዊ ድርጅት ማለት ነው።

## አንቀጽ 22

## ስለስምምነቱ ባለአደራ

የዚህ ስምምነት ባለአደራ የዓለም የአእምሯዊ ንብረት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ይሆናል።

ማራካሽ ስምምነት

ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

**Funded by USAID *Feteh* (Justice) Activity in Ethiopia**

*This document was produced and published with the support of the American people through the United States Agency for International Development (USAID). The content and opinions expressed in this document in no way reflect the views of USAID or the United States Government.*